# ሁለቱ ባቡሮች  የተለያዩ ናቸው

ከሚሊዮን አደም 12-8-14

እኔና ሳዲቅ በአንድ ወዳጃችን ቤት ለቅሶ ተቀምጠን ሳለ በእስር ላይ ስለሚገኙ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ችግር መፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴዎች ጉዳይ የውይይት ርዕስ ተነሳ  ውይይቱ በሰላም ተጀምሮ እንደውም የውይይት መሪ ተመርጦለት እጅ እያወጣን በሰላም ነው የተነጋገርነው

የተነሳው ብርቱ ርዕስ ኮሚቴዎቹ የተነሱለትና የታሰሩለት ዓላማ ተግባራዊ የሚሆንበት መንገድ ፤እነሱም ከነሙሉ ክብራቸው ስለሚፈቱበት ሁኔታ በአካሄዱ ላይ አሉ ስለምንላቸው ችግሮች አሁን በዲያስፖራው እየተደረገ ካለው ጥረት በተለየ መልኩ የሽምግልና ሂደት እንዲጀመር ፤ቀደም ሲል ከተለያየ ቦታ በተለያዩ ሽማግሌዎች በኩል በቡድንም ሆነ በተናጠል ተጀምረው በነበሩ ጥረቶች ላይ የነበሩ ድክመቶችን በመገምገም በውይይት ውጤት አመጣለሁ የሚል አካል ካለ ተመርቆ እንዲሸኝ ያለ ምንም መጠላለፍ የውይይት ሂደቱ ከመንግስት ጋር እንዲቀጥል የሚል ነበር

በነሳዲቅ በኩል ‹‹ መንግስት ከፍተኛ ውጥረት ውስጥ በገባበት ጊዜ መንግስትን በሀይል ወደ ድርድር እንዲመጣ ከማድረግ በስተቀር ምንም አይነት የሽምግልናም ሆነ የድርድር ሂደት በማንም አካል መጀመር የለበትም ›› የሚል ሀሳብ ተሰነዘረ

በኛ ወገን ደግሞ በአሁኑ ሰዓት ስለ ታሳሪ ኮሚቴዎቻችን ከመንግስት ጋር እተደረገ ያለ ውይይት ባለመኖሩ ውይይቱ ከመንግስት ጋር መቀጠል እንዳለበት ውይይቱ ሲደረግ ግን ኮሚቴዎቻችን ከታሰሩለት አላማ ጋር መጣጣም እንዳለበት ‹‹ ቀይ መስመር ›› ማስቀመጥ እንዳለብን ይኸውም ኮሚቴዎቻችን አሸባሪ እንዳልሆኑ ፤ በኢትዮጵያ እስላማዊ መንግስት ለማቋቋቋም እንዳልተንቀሳቀሱ መንግስትን በሀይል ለማፍረስ እቅድም ሆነ የተግባር እንቅስቃሴ እንደሌላቸው እስከዛሬ የተናገሩት የድምጽም ሆነ የቪዲዮ ማስረጃ ይህንኑ እንደሚያረጋግጥ ነገር ግን ከመንግስት ጋር ያላስማማቸው መጠነኛ ችግሮች ካሉ በውይይት እንደሚፈታ  ስለምናምን ፤ ስለዚህ ችግሮቹ ተፈተው  ከነ ሙሉ ክብራቸው በነጻ እንዲለቀቁና ለቀሪ ጉዳዮች ከመንግስት ጋር እንዲወያዩ  ይህ ሀሳብ የኛ ብቻ ሳይሆን የታሰሩት ኮሚቴዎችና የትግሉን ሂደት በበላይነት የሚመራው የድምጻችን ይሰማ ሃሳብ በመሆኑ አጀንዳ ሆኖ እንዲቀርብ ሀሳብ ስናቀርብ

በነ ሳዲቅ ወገን ግን  ‹‹ መንግስትን በሀይል ከማስገደድ ውጭ ሌላ የሽምግልና ሂደት መጀመር የለበትም ›› የሚለውን ሀሳብ አጠናክረው ገፉበት

ለነገሩ ሳዲቅ ከራሱ ሀሳብ ጋር የሚጣላ ሆኖ እንጂ በውይይታችን ወቅት ከግል የፌስ ቡክ ገጹ ላይ ውይይት በየትኛውም ሁኔታና ጊዜ መደረግ እንዳለበት የሚገልጽ ጽሁፍ አንብቦልን ነበር

እንደውም ሲያጠናክረው የፍልስጤሙ ሃማስ እና እስራኤል በውግያ ላይ እያሉ እንደሚደራደሩ አክሎበታል  እኛም የጎረቤታችን ደቡብ ሱዳን ተቀናቃኞች እየተዋጉ አዲስ አበባ ላይ እንደሚደራደሩ አጠናከርን

በኛ ወገን ሀሳባችንን መንግስት ይቀበላል አይቀበልም ውጤቱ ወደፊት እንደሚታይ ትግሉ አሁንም ቀላል እንዳልሆነ አንዱ በር ቢዘጋ ሌላውን እያንኳዋኩ ጥረቱን መቀጠል አስፈላጊ በመሆኑ ዝም ከማለትና በሩቅ ከመታኮስ ወይም ለመንግስት የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ክፍተት

ከሚሰጥ የትግል ስልት ለየት ባለ መንገድ እንድንሄድ ማንም አካል ‹‹ ከተሳካላቹ ሞክሩት ›› ብሎ መርቆ እንዲሸኘን እንጂ እንዳይጠልፈን የሚል ሃሳብ ሰነዘርን ይህን ያልንበት ዋና ምክንያት ካለን ልምድ እንደምናውቀው ከዚህ በፊት በአካሄዱ ላይ አንዳንድ ችግሮች ቢኖሩበትም ከቅን ልቦና በመነሳት አንዳንድ ቡድኖችና ግለሰቦች ኮሚቴዎቻችንን ለማስፈታት ያደረጉት ጥረት ‹‹ እነ እገሌ አዲስ አበባ የሄዱት ኮሚቴዎቹን ይቅርታ ጠይቁና ውጡ ሊሉ ነው ›› ወዘተ ሲባል እንደሰነበተ እናውቃለን

እነዚህ ቡድኖች ብዙ አደናቃፊ ነገር እያጋጠማቸውም ቢሆን ቢያንስ እስረኞችን ዘይረው ለሌላ ቀጣይ ጉዞ የሚሆን የትግል እርሾ ይዘው ተመልሰዋልና አላህ የኀይር ጀዛቸውን ይክፈላቸው

የአብዛኛው የውይይቱ ተሳታፊ ሃሳብ ውይይት አስፈላጊ መሆኑ ነገር ግን ፍርሃታቸው መንግስት ኮሚቴዎቹን ይቅርታ ጠይቁና ውጡ ቢላቸው ይህንን ሃሳብ እንዳንቀበል የሚያሳስብ ነበር

በዚህም ውይይቱ አብቅቶ ሳዲቅም በዲያስፖራው አብረው ለሚሰሩ አካላት ይህንኑ እንዲያሳውቅ እና እንድንነጋገርበት ተስማምተን ስንለያይ ምሽቱ ዝናብ እያካፋ ስለነበር ራቅ አድርጌ ወዳቆምኩዋት መኪናዬ ያደረሰኝ ሳዲቅ ነበር

ወዳጄ ሳዲቅ በማግስቱ ደውሎ በትናንት ማታው ውይታችን አለመደሰቱን በሚያሳብቅ ድምጽ በ ቢቢኤን ራዲዮ ስለ ሽምግልና ሂደት ፕሮግራም ሊሰራ እነደሆነ ነገረኝ

‹‹ እናንተ ኮሚቴዎቻችንን ለማስፈታት ይሆናል ይቻላል የምትሉትን ጥረት አድርጉ አላህ ይርዳቹ ከናንተ ሂደት በተለየ መልኩ መፍትሔ እንፈልጋለን የናንተን አካሄድ አልወደድነውም ያሉ አካላትን ግን አታደናቅፉ ስማቸውንም አታጥፉ የጋራ ግባችን አንድ ነው በድምጻችን ይሰማ የሰላማዊ ትግል አቅጣጫ የእስልምና መብትን ማስከበርና በዚህ ሐሳብ ምክንያት የታሰሩትን ማስፈታት ነው

ለምሳሌ እኔ በኢትዮጵያ በሰላማዊ መንገድ በምርጫ እንሳተፋለን የሚሉ አካላት ምርጫ ቦርድ ከመንግስት ተፅዕኖ ሙሉ በሙሉ ሳይወጣ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ምቹ የመወዳደርያ ሜዳ ሳያገኙ በኢትዮጵያ በምርጫ መሳተፍን አላምንበትም ዴሞክራሲያዊ ምርጫም ይደረጋል ብዬ አላምንም ነገር ግን እኔ ስላላመንኩ ‹‹ አይ በምርጫ ተወዳድረን ለውጥ እናመጣለን የሚሉ የፖለቲካ ድርጅቶች ካሉ ግን የመረጡትን መንገድ ልከለክላቸው አልችልም ›› ብዬ በምሳሌ አስረዳሁት

መሽትሽት ሲል በቢቢን ራዲዬ ‹‹ ዳሰሳ ›› በሚለው የፕሮግራም ክፍል ስለ ሽምግልና ሂደት የተሰራውን ፕሮግራም ሊንክ እንድሰማው ቴክስት አደረገልኝና ሰማሁት በውይይታችን ወቅት ካነሳናቸው ነጥቦች ሌላ ብዙም የተለየ ሀሳብ አለየሁበትም ወደ ሽምግልና እንሄዳለን የሚሉ አካላት ማድረግ ስላለባቸው ጥንቃቄ መንግስት በሽምግልና ስም ሊሰራ ይችላል ብሎ ስለሚያስበው ደባና ሻጥር የሚገልጽ ነበር

ኖቬምበር 22.2014 ጠዋት በውይይቱ ላይ የነበረ አንድ ወዳጄ ስልክ ደውሎ በኢካዴፍ ድረ ገጽላይ በሳዲቅ አህመድ ተጽፎ ስለወጣው ጽሁፍ ነገረኝ

‹ሽምግልና የህወሃት የጥቃት ደመና ›በሚል ርእስ የውጣውን ጽሁፍ አየሁት እንዲህ ይላል

‹‹ የኢትዮጵውያንን ሰላማዊ ትግል በሃይል ለመቀልበስ ያልቻለው ህወሃት መራሹ መንግስት የሙሰሊሙን ጉዞ ለማፋለስ የተለያዩ ሴራዎችን ያሴራል ›› ብሎ ይንደረደርና ይህንን ለማስፈጸም በዲያስፖራው ያሉ ‹‹ በሱስ የተጠመዱ የራሴ የሚሉት ስራ የሌላቸው ከባለስልጣናት ጋር ቀረቤታ ያላቸው ሃገር ቤት የሚመላለሱ ሀገር ቤት ሆነው ባምባገነናዊው

ስርዓት ተጠቃሚ የሆኑ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች የሚያደርጉት ትግል ያላችውን መረጋጋት የነካባቸው ስርዓቱ ሊናድ ይችላል የሚል ፍራቻ ያላቸውና በሽምግልና ስም ይህንን አምባገነናዊ ስርአት ለማቆየት እየተርዋርዋጡ ነውና እንዳትስሙዋቸው የሚል መንፈስ ያለው ነው

እኛ የዚህ የሽምግልና ሂደት መቀጠል አለበት የምንል ግለሰቦች ለዚህ ሽምግልና ሂደት የምንርዋራጥበትና የምንደክምበት ዋና ምክንየት እውነት ሳዲቅ እንደሚከሰን ስራ ፈት ስለሆንን በሱስ ስለተጠመድን ወይም ይህንን መንግስት ከመናድ ልንከላከል የቆምን ፤ ይሄ መንግስት ቢናድ ጥቅማችን ስለሚነካም አይደለም ይልቁንም የታሰሩት ኮሚቴዎች ትግሉ ከተጀመረ ጀምሮ መንግስት እንደሚከሳቸው አንድም ቀን በኢትዮጵያ እስላማዊ መንግስት ለማቁዋቁዋም እንዳልተንቀሳቀሱ መንግስትን በሃይል ለመጣል ሃሳብ እንደሌላቸው በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ምንም አይነት የሽብር ጥቃት ለመጣል ወይም ለማስጣል ሃሳቡም እቅዱም ሆነ ድርጊቱ እንዳልታየባቸው ይልቁኑ የኢትዮጵያ ሙስሊሞችን መብት ለማስከበር በተለይም ሶስት መሰረታዊ ጥያቄዎችን በማንሳት ይህንንም ሰላማዊና ሰላማዊ በሆነ መንገድ ብቻ ለማስፈጸም ትግሉን እንደጀመሩ ለዚህም ብለው አለአግባብ ለእስር እንደተዳረጉ አሁንም ከዚህ አቁዋማቸው ስለመቀየራቸው የሚያሳይ ምንም ማስረጃ ስለሌለን ‹‹የሰላማዊ ሂደቱ አብቅቶለታል ትግላችሁን መንግስትን በሃይል ወደማንበርከክ አሸጋግሩት ›› ብለው የጻፉት ደብዳቤም ሆነ የድምጽ መልዕክት ስለሌለን ውጭ ያለን ሰዎች የድምጻችን ይሰማ ተከታዮች በመሆናችን ድምጻችን ይሰማም ‹‹ ትግሉን መንግስትን ወደመቀየር ለውጡት ስላላለን በየትኛውም ሚዲያ በጠበቆቻቸው በኩል ይሄው ስላልተገለጸልን እኛ እዚህ በሞቀ አልጋ እየተኛን ከልጆቻችን ጋር እየተጫወትን እነሱ ለዚህ ክቡር ዓላማ መስዋዕት ሆነው አለአግባብ ለእስር ተዳርገው ያሉበት ሁኔታ ዘወትር እረፍት ስለሚነሳን ፤ በነሱ እስር መራዘም ጉዳት እንጂ ጥቅም ስላላገኘን ነው አንዱ በር ሲዘጋ ሌላውን እያንኩዋኩዋን ዘወትር ከመንግስት ጋር ለውይይት እምንዘጋጀው

‹‹ መንግስት አገሪትዋን ማስተዳደር አልቻለም የህዝብን መብት ማስከበር አቅቶታል ከስልጣን መውረድ አለበት ›› የሚል አካል ካለ እንደማንኛውም ስለ ሃገሩ እሚመለከተው ኢትዮጵያዊ በሌላኛው የትግል ባቡር ተሳፍሮ ትግሉን መቀጠል መብቱ ነው ይኽንን እኛ ልናቆመውም ሆነ ልንከለክለው አንችልም

ነገር ግን ይህኛው ትግል የሃይማኖት መብቶችን ለማስከበር ዓላማ ያደረገ የትግል ስትራቴጅውም ግልጽና በይፋ የተገለጸ ሆኖ ሳለ ይህንን ጉዳይ በዲያስፖራው አካባቢ በባለቤትነት ይዘው ትግሉን እንመራለን የሚሉ አካላት የሚከተሉት መንገድ እኛና ድምጻችን ይሰማ ከሚያስበውና ኮሚቴዎቹ ካስቀመጡትና ከታሰሩለት መንገድ ውጪ በመሆኑ ይህ ከፍተኛ የሃሳብ ልዩነት ተከስቶአል ምክንያቱም ሁለቱ ባቡሮች የተለያዩ ናቸውና

በመሰረቱ በማንኛውም ጉዳይ ላይ የተለየ ሃሳብ መያዝ ወንጀል አይደለም ይህንንም መቃወም የነጻ አስተሳሰብ ነጸብራቅም አይደለም

እኛ ለዚህ ትግል የተለየ ሃሳብ አለን ስላልን ስራ ፈቶች በሱስ የደነዘዙ ይሄ መንግስት ቢወድቅ ጥቅማቸው የሚነካ ኢትዮጵያ የሚመላለሱ ከባለ ስልጣናት ጋር ቅርበት ያላቸው ወዘተ የሚል የስድብ ናዳ አወረደብን

በመሰረቱ በውይይቱ ላይ ከነበሩት አንዳንዶቹ ካንድም ሁለት የግል ንግድ ድርጅት ያላቸው ለታሳሪ ቤተሰቦቸህ ገንዘብ ሲሰባሰብ ቦረሳዬን ቤት ረስቼው መጣሁ ሳይሉ ከማንም በላይ የበለጠ ድጋፍ ያደረጉ አሁንም እያደረጉ ያሉ የቤተሰብ አስተዳዳሪ ጨዋ ሙስሊሞች መሆናቸውን አውቃለሁ

በሱስ የደነዘዙ የተባሉት መቼም ሙሲሊሞች ናቸውና የመጠጥም ሆነ የሃሽሽ ሱሰኛ ሆነው የደነዘዙ ናቸው አልልም

እኛም ቤተሰብ የምናስተዳድር በአሜሪካ የኑሮ ጥድፍያ ጊዜ ያልተረፈን ታታሪዎች ነን

ለዚህ ጽሁፋቸው እንኩዋን መልስ ለመስጠት ስንት ቀን እንደፈጀብን ልብ ይሉዋል

መቼም እንደኔ የጽሁፍ ችሎታ ስለሌላቸው ነው እንዳይል የአሜሪካ የጥድፍያ ኑሮ አላላውስ ቢለን እንጂ ስለ ጽሁፍ ችሎታው ለዚህ የማያንስ እውቀት ከአላህ እንደተሰጠን ከሳዲቅ በላይ ምስክር የለም

መንግስትን የሚደግፉ ላለው ጉዳይ መንግስትን የሚደግፉ ሊኖሩ አይችሉም ብዬ ልከራከር ባልችልም በሌላኛው ወገን ደግሞ የሙስሊሙ መሪዎቻችንና ድምጻችን ይሰማ ከሚሉት የትግል ስልትና ስትራቴጂ ውጪ ሌሎች ሃይሎች በራሳቸው ምክንየት መንግስትን ለመጣል በተሳፈሩበት ባቡር ተሳፍረው የግል አጀንዳቸውን የሚያራምዱ ሊኖሩ አይችሉም ብዬም ከመጠርጠር አልቦዝንም

ሳዲቅን ጨምሮ መንግስት 99.6 ፐርሰንት ምርጫ አሸነፍኩ ሲል በአባይ ግድብ ግንባታ ስም 99.6 ፐርሰንት የምርጫ ውጤትን ደግፈው መፈክር ይዘውና ሰማያዊ ቲ ሸርት ለብሰው በአሜሪካ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ፊት ለፊት የኢትዮጵያን መንግስት ደግፈው ሰልፍ የወጡ የነሳዲቅ ጎራ አባላት መኖራቸውን አውቃለሁና ምነው ታድያ ለነዚህኞቹ የመንግስት ደጋፊነትን ነፈጋቸው ነው ወይስ እነ ሳዲቅ በሚደግፉት ጊዜ መንግስት ለህዝባችን ከሰማይ መና ያወርድ ነበር

የሆኖ ሆኖ ለመንግስት ያለን ድጋፍም ሆነ ተቃውሞ ከዚህ ትልቅ አጀንዳ ጋር የሚያያይዘው ምንም ምክንያት የለም መንግስትን መደገፍም ፣መቃወምም ፣መውቀስም ሆነ ማመስገን መብት ነው

በኛ እምነት መንግስት ለዚህም ድርድር በር የከፈተልንና ጆሮ የሰጠን እነ ሳዲቅ እንደሚፎክሩት መንግስትን ስላንበረከኩትና ስለፈራቸው ሳይሆን የኮሚቴዎቹን ሰላማዊነትና ባስቀመጡት የትግል ስልት ብቻ እየተንቀሳቀሱ መሆኑን አውቆ ፣በእስር ቤትም ያላቸውን ስነ ምግባርና ጽናት አይቶ እንጂ ባያጠፉም አስራ ስምንት ፣ ሃያ አምስት ዓመት ወይም እድሜ ልክ እስራት መፍረድ ስላቃተው አይደለም

ስለዚህ የነሳዲቅ ወገኖች የኮሚቴዎቹን ጉዳይ በፍርድ ቤት የጥብቅና ውል ሞልተው ውክልና እንደተሰጣቸው ጠበቆች ያለኛ እሚመለከተው የለም እኛ እንዳሻን እንዘውረዋለን ከሚል ጨለምተኛ አመለካከት ወጥታችሁ ጉዳዩ የጋራ አላማውም አንድ መሆኑን አውቃቹ ሰዎች በነጻነት ሲንቀሳቀሱ እንቅፋት እንዳትሆኑ እንመክራለን እናንተ እንደምትሉት እውነት መንግስትን በሃይል ካንበረከካቹት ይሄ መንግስትም ሊወድቅ አንድ ሃሙስ ከቀረውና እስረኞቹን እምታስፈቱ ከሆነ ጥረታችሁን ቀጥሉ አላህ ይርዳቹ ለመንገዳችሁም መሰናክል አንሆንም

እኛ ደግሞ እውነት እናንተ እንደምትሉት ይሄ መንግስት ሊወድቅ የተቃረበ ቢሆንና በናንተ ትግል አካሄድ የተንበረከከ መሆኑን ብናምን ከሚወድቅ መንግስት ጋር የምንደራደር ሞኝ ከናንተ ያነስ ጭንቅላት ያለን ደደቦች እንዳንመስላቹ

ይልቁኑ ሊወድቅ ከተቃረበ መንግስት ጋር ከመወያየት ይልቅ ከአንበርካኪዎቹ ከናንተ ጋር ማበሩ ይበልጥብን ነበር

በዚህ አጋጣሚ እስረኛ ቤተሰቦችን በመደገፍ ታሳሪዎች አንገታቸውን እንዳይደፉ ጥንካሬ ሆናቹ ደከመን ሰለቸን ሳትሉ በገንዘብ እየረዳቹ ያላቹ ከሁሉም የሚበልጠው የናንተ ትግል ነውና አላህ ጀዛ ይክፈላቹ ለገንዘባችሁም በረካ ይስጣቹ የኔም ሰላሳ ዶላር አለበትና ዱኣ አርጉልኝ ወደፊትም በአቅሜ ድጋፌን ለመቀጠል ቃሌን አድሳለሁ

እነ ሳዲቅም የአለምን ነባራዊ ሁኔታን አገናዝባቹ በጊዝያዊ ጭብጭባ ሳትኮፈሱ ለችግሩ እውነተኛ መፍትሂ እንድታመጡ ከድምጻችን ይሰማ የትግል ስልት ሳታፈነግጡ የመሪነት ሚና ለመጫወት ሞክሩ

ዝሆኖች ሲጣሉ ሚጎዳው ሳሩ ነውና በኛና በናንተ መጠላለፍ ምክንያት ክቡር አላማ ይዘው ለእስር የተዳረጉ ኮሚቴዎቻቸችንን የስቃይ ጊዜ አታራዝሙ ምናልባት የነሱ እስር መራዘም የናንተን ገቢ የሚያሳድገው ከሆነ ገቢው ይቅርባቹ

ለዛ ይሆን እንዴ በውይይታችን ወቅት አንዱ ተሳታፊ ‹‹ እውነት ከልባችሁ እንዲፈቱ ትፈልጋላቹ ወይ ›› ብሎ የጠየቀህ መልሱን ለህሊናህ ትቼዋለሁ

የሳዲቅ ጽሁፍ የግል አቋዋሙ ብቻ ይሁን አይሁን ማረጋገጥ ባልችልም በዲያስፖራው የታሳሪ ኮሚቴዎችን ጉዳይ የያዙ አካላት ይህንን በስድብ የታጨቀ ጽሁፍ አይተው ምንም ካለማለታቸውም  ሌላ በሚያስተዳድሩት ድርጅት ዌብ ሳይት ላይ በማውጣታቸው ካለነሱ እውቅና እንዳልተደረገ ስለምገምት ይህ አስተያየት እነሱንም የሚመለከት ይሆናል

ሁሉም በልቡ ለነየተው መልካም ነገር አላህ እንደልቡ ይክፈለው

ኮሚቴዎቻችንም የተነሱለት አላማ እንዲሳካ እነሱም ከነ ክብራቸው ከእስር እንዲወጡ አላህ ይርዳን

---------------------------------

ለዛሬ  ጽሁፌ መነሻ  የሆነኝ ኖቬምበር 22/2014 በECADF  ድረገጽ ላይ በወዳጄ ሳዲቅ አህመድ ‹‹ ሽምግልና የህወሃት የጥቃት ደመና ›› በሚል ርዕስ የተፃፈው ፅሁፍና ስለዚሁ ጽሁፍ በኢሳት ራዲዮ የሰጠው ትንታኔ ነው

ይህ ጽሁፌን  በዚህ ድረገጽ እንዳወጣው ያስገደደኝ

1ኛ  ኢካዴፍ ድረገጽ ላወጣው ፅሁፍ  ምላሽ መስጠት እንድንችል ባስቀመጠው ክፍት ቦታ ላይ ይህንን ጽሁፍ ብልክላቸውም  ጽሁፉን ባለማውጣታቸው

2ኛ ለምን እንዳላወጡት ምላሽ እንዲሰጡኝ በ ኢሜይል አድራሻቸው  infoatecadforum.com ብጽፍላቸውም መልስ ስላልሰጡኝ

3ኛ ኢሳት ራዲዮ ኖቬምበር 25 2014 ላስተላለፈው  ፕሮግራም ምላሽ እንዳለኝ  ኖቬምበር 26 2014 ከጠዋቱ 9.30 AM  ስሜንና ስልክ ቁጥሬን በድምጽ መቀበያ ሳጥናቸው ውስጥ ብተውላችውም ምላሽ ስላልሰጡኝ ነው

ወደ ዋናው ጉዳያችን እንግባ